የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ - በርሊን

Embassy of the Federal Democratic
Republic of Ethiopia - Berlin

ቀን፡ ሰኔ 3 ቀን 2007 ዓ.ም.

ቁጥር፡-በኢኤ/24-1/399/07

በጀርመንና በተወከልንባቸው ለምትኖሩ የዲያስፖራ አባላት በሙሉ

ጉዳዩ፡-<u>ኢ.ኤ.አ ከአገስት 3 -10/2015 የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ፌስቲቫል እንደዚሁም ኢ.ኤ.አ ከአገስት 12 -17/2015 በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከበረው የኢትዮጵያ የዲያስፖራ ቀን በዓል አከባበር ላይ ለመሳተፍ ለምትፈልጉ የዲያስፖራ አባላትን ይምለከታል፤</u>

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት ኢ.ኤ.አ ከአገስት 3 - 10/2015 ዓ.ም. የሚከበረው የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል የዲያስፖራ ፌስቲቫል ሳምንት ምክንያት በማድረግ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የትኬት ዋጋ ቅናሽ ትብብር እንዲያደርግ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጠየቀው መሠረት 40% እና 15% የትኬት ዋጋ ቅናሽ እንደሚያደርግ አሳውቋል፡፡

ስለሆነም ለበዓሉ ድምቀትና በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ገብተው የእድገትዋንና የትራንስፎርሜሽን ተካፋይ እንዲሆኑ አየር መንገዱ በተስማማው በተወሰነ ጊዜ የዋጋ ቅነሳ መሠረት ለተወሰኑ የመቀመጫ ብዛቶች ከ40% እስከ 15% ቅናሽ በማድረግ በሚከተሉት ደንብና ሁኔታዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፈቅዷል፡፡

1. እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከጁን 3 እስከ ጁን 20/2015 ዓ.ም. ለሚገዙ ቲኬቶችና ከጁላይ 29 እስከ አገስት 3/2015 እስከ ተጓዙ ድረስ 40% ቅናሽ ለመስጠት፣
2. ከላይ ከተጠቀሰው የጉዞ ቀናት ውጪ ለሆኑ ጉዞዎች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር እስከ ጁን 30 ቲኬቶቹ እስከተገዙ ድረስና በቡድን ለሚጓዙ ከአስር ሰው ያላነሱ የቡድን ተጓዦች 15% ቅናሽ የሚሰጥ መሆኑን፤
3. የሻንጣ መጠን 2PC/32 ኪሎ ለእያንዳንዱ መንገደኛ የሚሰጥ መሆኑን፤
4. ማንኛውም መንገደኛ ይህንን ቅናሽ የሚያገኘው የአዘጋጁን የትብብር ደብዳቤ ሲያቀርብ ብቻ መሆኑን፣
5. ይህ የቅናሽ አገልግሎት የሚሰጠው ሽያጩ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ቢሮዎች ብቻ መሆኑን አየር መንገዱ በጻፈልን ደብዳቤ ገልጿል፡፡

በዚሁ መሠረት ሁሉም የዲያስፖራ አባላት የተሰጠውን እድል በመጠቀም ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ የምትፈልጉ ሁሉ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክነውን የመመዝገቢያ ቅጽ በመሙላት በአስቸኳይ እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ኤምባሲ
በርሊን

ደምሴ ከበደ
አማካሪ II

<u>አባሪ</u>፡- የመመዝገቢያ ቅጽ

Boothstrasse 20a
12207 Berlin

Telefon: 030-772 06-0
Telefax: 030-772 06 26
E-Mail: Emb.ethiopia@t-online.de

Consulate: Telefax: 030-772 06 24
E-Mail: Consulberlin.eth@t-online.de
www.aethiopien-botschaft.de